# መመሪያ

የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

| | |
|---|---|
| ተዛማጅ መመሪያዎች/ደንቦች:- | ABA, ABC, ABC-RA, ACA, ACA-RA, AEB, GEG-RA, IFA, IFA-RA, IKA, IKA-RA, IOA, IOA-RA, IOB, IOD, IOD-RA, ISB-RA, JEA-RA |
| ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት:- | ዋና የአካደሚ መኰንን |

## ቀዳሚ የህፃናት/የልጅነት እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማዕቀፍ/Framework እና መዋቅር/Structure

### A. ዓላማ

ልጆች በቀደምት የትምህርት ዕድሜአቸው በአእምሮ እውቀት፣ በማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና በአካል እድገትና መዳበር በከፍተኛ ጥራት፣ በተገቢው ሁኔታ እንዲዳብር፣ ፈታኝ እና ሁሉን አቀፍ ቀዳሚ የህፃናት/የልጅነት እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራሞችን ለማስፋፋት የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድን ጠንካራ እምነት/ቁርጠኝነት ለማረጋገጥ

ከወላጆች/ሞግዚቶች በጋራ እና ከማህበረሰቡ ባለድርሻ አካላት የካውንቲውን የመንግስት አስተዳደር፣ እና ስቴት እና የአካባቢ ኤጀንሲዎችን ጨምሮ በጋራ ትብብር፤ ለእያንዳንዱ ልጅ ከፍተኛ ጥራት ያለው የልጅነት እድሜ ልምምድና ቁልፍ የሆነ የእድገትና የትምህርት ጠንካራ መሠረት የሚፈጥር፣ በእያንዳንዱ ተከታታይ የክፍል ደረጃ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ወደ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እያደጉ በሚሄዱበት ጊዜ የአካደሚና የግል የህይወት መከናወን እንዲኖራቸዉ የሚያስችል ቀዳሚ የሕጻናት/የልጅነት እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማእቀፍ ለመመስረት።

የቀደምት መለያና ተለይተው ለታወቁ ልጆች የጣልቃ ገብነት ስልቶችን ለማቅረብ

በመረጃ የተሞረኮዘ፣ ከአስተዳደግ ጋር የሚመጥን/የሚጣጣም ሥርአተ ትምህርት/ከሪኩለም እና የማስተማር ተሞክሮዎች በአጋዥ እና ባህላዊ ብቃት ባለው የትምህርት ምህዳር/ድባብ ዉስጥ፣ በቤተሰብ እና በማህበረሰብ ተሳትፎ፣ በሠራተኛ ሙያ ማዳበር፣ እና ከቀዳሚ የልጅነት ትምህርት ፕሮግራሞች እና የማህበረሰብ አጋሮች ጋር በመተባበር፣ የማህበረሰብ የልጆች እንክብካቤ ማዕከላትን፣ የቤተሰብ የልጆች እንክብካቤ ቤቶች፣ እና የግል ቀዳሚ ት/ቤቶች ን ባካተተ መልኩ ለቀዳሚ የሕጻናት/የልጅነት እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚጠበቀውን ማዘጋጀት።

### B. ጉዳዩ

በቀዳሚ የልጅነት እድሜ እና በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ዓመታት ፕሮግራሞች ለወደፊት ወደ ከፍተኛ ደረጃ የትምህርት ውጤታማነት/ስኬታማነት እንደሚያመራ እያደገ የመጣው ጠንካራ የሆነ መረጃ ያመለክታል። የካውንቲውን፣ የስቴት፣ እና የፌዴራል መገልገያዎችን/resources ከማህበረሰብ አጋሮች ጋር በአግባቡ በመጠቀም ለወጣት ልጆች እና ለቤተሰቦቻቸው በጣም ተፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ለመቀጠል የተለየ አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ልጆች ለመለየትና የተማሪ እድገትን ለማመቻቸት፣ ሽግግር፣ ምደባ፣ እና የፕሮግራም ቀጣይነትን በእያንዳንዱ የልጅ የእድገት ደረጃ፣ ከቤት፣ ከልጆች እንክብካቤ/ማሳደጊያ፣ ወይም ቀዳሚ የሕፃናት ት/ቤት እስከ ሙዓለ ህፃናት (pre-K)፣ እንደአግባብነቱ፣ እና ከአንድ የኤለመንተሪ ደረጃ ወደ ሌላኛው ድረስ ለማሳካት የቦርዱ ጠንካራ እምነት ነዉ ።

ቦርዱ በመላው የሞንጎመሪ ካውንቲ ልጆችን በቀዳሚ የልጅነት እድሜአቸው ከተወለዱበት እስከ አምስት ዓመት እና ለኤለመንተሪ ት/ቤት ስኬታማነት ለማዘጋጀት በሞንጎመሪ ካውንቲ ቀዳሚ እንክብካቤ እና የትምህርት ስትራተጂ ላይ በተዘረጋው መሠረት ከህዝባዊና የግል ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር ይሠራል።

ከእነዚህ የማህበረሰብ አጋሮች ውስጥ፣ የሞንጎመሪ ካውንቲን ብዙ ስብጥር የወጣት ተማሪዎችን ፍላጎት ለማሟላት የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS') ሚና የስቴት እና የፌደራል ህጎችን መመዘኛና መስፈርቶችን ለሚያሟሉ ገና ወደ ሙዓለ ሕፃናት እድሜ ላልደረሱ ህጻናት ቀዳሚ ጣልቃገብ እና የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን መስጠት ነው። ቀዳሚ ጅማሪ/ሄድስታርት እና pre-K ፕሮግራሞች የገቢ-አቅማቸዉ ለሚፈቅድላቸው ልጆች በሙዓለ ህፃናት እና ከዚያም በላይ ለሆነ መሠረታዊ እውቀትና ክህሎት ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት ተሞክሮዎችን ይሰጣል። በተጨማሪ፣ ጁዲት ፒ. ሆየር ቀዳሚ የህፃናት እንክብካቤ እና የቤተሰብ ትምህርት ማዕከሎች (Judith P. Hoyer Early Child Care and Family Education Centers)፣ ወይም የ ጁዲ ማዕከሎች (Judy Centers) ከስቴት በተመደበ ገንዘብ እና ከአካባቢ በሚመደብ/በሚገኝ ገንዘብ የሚንቀሳቀስ ቀዳሚ የልጅነት እና የቤተሰብ ትምህርት ማዕከሎች ለህጻናት ከተወለዱበት ጊዜ አንስቶ እስከ አምስተኛ ክፍል ድረስ አጠቃላይ ቀዳሚ የህፃናት ትምህርት አገልግሎቶችን ይሰጣል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለልጆች የተለያዩ ዓይነት ማጣሪያዎችን፣ አስቀድሞ ጣልቃ ገብ አገልግሎት፣ እና የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ከተወለዱበት ጊዜ አንስቶ እስከ ስምንት ዓመት ድረስ፣ በቤታቸውና በት/ቤት መሠረት ያደረጉ ፕሮግራሞች እና ሌሎችም በአካባቢና ማእከል ፕሮግራሞች ይሰጣል። ለልጆች በስፋት አገልግሎቶች የሚሰጡት ባላቸው ፍላጎት መሠረት በተለያየ ደረጃ ስለ ንግግር/ቋንቋ፣ የመስማት/ማዳመጥ፣ የማየት፣ የሰውነት መገጣጠሚያ/orthopedic እና የእድገት ዘገምተኝነትን ጨምሮ በተለያየ አይነት ፍላጎቶች ሲሆን ነገር ግን በዚህ ብቻ አያበቃም።

ከ pre-K፣ ሙዓለሕፃናት፣ እስከ 3ኛ ክፍል ድረስ ቀደምት የልጆች ትምህርት ፕሮግራም ጅምረው ሳያቋርጡ መቀጠል አስፈላጊ/ጠቃሚ መሆኑንና ከ3ኛ ክፍል በላይ ላሉት አንደኛ ደረጃ ክፍሎች ለአካዴሚያዊ ዝግጁነት አስፈላጊ ዓብይ እመርታ እንደሚሆን ቦርዱ አረጋግጧል።

የትናንሽ ልጆች ልዩ የአስተዳደግ ደረጃዎች እና ሥነ-ምግባሮች ቀዳሚ የልጅነትና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራሞች አፈጻጸም መተግበርን መምራት አለበት። የትናንሽ ልጆች አስተሳሰብ፣ የመማር ዘይቤዎች፣ እና ስለዓለም ያላቸው አመለካከት ከትላልቅ ልጆችና ከጎልማሳ ሰዎች በዓይነቱ ይለያል።

ምንም እንኳን ትናንሽ ልጆች እንደ ቡድን ተመሳሳይነትን የሚጋሩ ቢሆንም፣ እርስ በርሳቸው በጣም ልዩነት ስለሚኖራቸው፣ አግባብነት ያለው የመርሐግብር ዝግጅት እያንዳንዳቸውን ለመቀበል ምቹ ናቸው። የቤተሰብ ሁኔታ፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ ፆታ፣ ማንነት፣ የትምህርት ዘይቤ፣ ፍላጎቶች፣ እና ችሎታ/ክህሎቶች ስለ ልጅ ግላዊ ማንነት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። አብዛኛዎቹ ልጆች ተመሣሣይ የእድገት ደረጃዎችን ሊያልፉ ይችላሉ፣ ነገር ግን የአስተዳደግ ፍጥነት/እመርታ ከልጅ ወደ ልጅ ይለያያል። ይልቁንም፤ አስተዳደግ/እድገት አብዛኛውን ጊዜ እኩል አይሄድም። የግንዛቤ፣ የአካል፣ የማህበራዊ እና የስሜት የብስለት ደረጃዎች በእያንዳንዱ ልጅ ዉስጥ ሊለያይ ይችላል።

ቀዳሚ የህፃናት እና የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ፍላጎቶችን የሚያሟላ ጥብቅ የትምህርት መርሃ ግብር ለመመስረት እና ለማቆየት/ለማዝለቅ የሚከተሉት ኤሌመንቶች/ነገሮች አስፈላጊዎች ናቸው፡-
አጠቃሎ የያዘ ሥርዓተ ትምህርት/ካሪኩለም እና ተዛማጅ መመዘኛዎች፣ ጥብቅ፣ የተለየ ዓይነት የማስተማሪያ ፕሮግራም፣ ዓላማ ያላቸው የጨዋታ ዕድሎች፣ ትክክለኛ ሠርተፊኬት የያዙ፣ የሥራ ፈቃድ ወይም የሙያ ማረጋገጫ ያላቸው ቁርጠኛ/ትጉህ ሠራተኞችና አመራር፣ ተባባሪና እንደየሁኔታው የሚያስተካክል ድርጅታዊ መዋቅር፣ እና ሙሉ ተሳትፎ የሚያደርጉ ወላጆች/ሞግዚቶች እና የማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት።

C. **አቋም**

1. ቀዳሚ የልጆች ፕሮግራም እና የት/ቤት ባህል

   እያንዳንዱ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩል (MCPS) የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የልጆችን አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ቋንቋ፣ ስሜታዊ፣ እና ማህበራዊ እድገት፣ ግላዊ ሐቀኝነት፣ በራስ መተማመን፣ የማህበረሰብ ኃላፊነት፣ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር እርስበርስ መከባበር፣ እንዲሁም መነቃቃት፣ እና ለመማርና የተሻለ ለመሆን/ለመመንጠቅ የመጓጓትን ባህል እንደሚከተለው ያዳብራል፡-

a) የሁሉንም ወጣት ተማሪዎች ተፈጥሮአዊ የማወቅ ጉጉት/ፍላጎትና የፈጠራ ችሎታን በንቃት ለመዳሰስ፣ አዲስ ግኝት፣ እና አእምሮን በሚገዳደር ሙከራና ልምምድ እውቀት እንዲገነቡ እና በሚጋብዝ፣ በሚያነቃቃ፣ እና ድጋፍ ሰጪ የሆነ የመማር ሁኔታ ጋር መጎዳኘት ይኼውም፡-

(1) የትምህርት ቁሳቁሶችን በራሳቸው ፍላጎት እየመረጡ እና እንደአግባቡ በራሳቸው እየተመሩ ለመማር በንቃት እንዲሳተፉ ማደፋፈር/ማበረታታት።

(2) ገንቢ የሆነ መዳፈርን ያበረታታል እና ስህተቶችን እንደመማሪያ መሣሪያ ይጠመቀማል፣ እና

(3) ወጣት ልጆች ለመማር የሚያስችላቸውን ያክል ቀጣይ ጊዜ ይሰጣቸዋል።

b) በልጆች መካከል እና በአዋቂዎችና በልጆች መካከል ቀና የሆነ መልካም ግንኙነትን ለማደፋፈር በደንብ-የሚመራ/የሚተዳደር፣ ሠላማዊና፣ የበለፀገ አካባቢ እንዲኖር ማድረግ።

c) በእያንዳንዱ ቀን በዓላማ ላይ የተመሠረተ ጨዋታ መስጠትና በጥቅሉ ለአእምሯዊ እና አካላዊ እድገት የሚጠቅም በእድሜአቸው ተመጣጣኝ ክፍል እና የመጫወቻ ቦታ መስጠት።

d) የጨዋታ ሜዳ፣ በሠፈር/ጎረቤት እየተራመዱ፣ እና በመስክ ጉዞዎች ትምህርት ለማግኘት የክፍል ውጪ አካባቢዎችን እንደ ጠቃሚ/ አስፈላጊ እድሎች መጠቀም።

e) ወላጆች/ሞግዚቶች የልጃቸው የመጀመሪያ አስተማሪ መሆናቸውን መገንዘብ፣ እና ለልጅ እድገትና ብልጽግና የወላጆች/የሞግዚቶች እና የቤተሰብን አስተዋጽኦ ልዩ መሆኑን መገንዘብ።

f) ከቦርድ ፖሊሲ/Board Policy ACA ጋር የሚጣጣም አድሎ የሌለበት፣ እኩልነት/ትፍትሃዊነት፣ እና የዳበረ ባህል፣ተግባቦትን፣ መከባበርን፣ እና በተማሪዎችና በሠራተኞች መካከል በፖሊሲው (Policy ACA) ላይ እንደተገለጸው በለግለሰባዊ ማንነት ላይ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚታሰብ ግላዊ ስነምግባር ላይ ያልተመሠረተ ባህላዊ ብቃት ማዳበር።

g) ግላዊ ኃላፊነት፣ ተዓማኒነት፣ እና ስነ ዜግነት አስተሳሰብን የሚያዳብር ማንነትን ለመገንባት ተጠባቂዎች እና የመመዘኛዎች ሥርዓት ማቅረብ።

h) ዲሲፕሊን/ሥነ ሥርዓትን የእድገት/የአስተዳደግ ሒደት አድርጎ መመልከት፣ ከቦርድ ፖሊሲ/Board Policy JGA ጋር በማጣጣም የተማሪ ዲስፕሊን ተገቢ ላልሆነ የተማሪ ሥነ ምግባር ወቅታዊ እና እድሜን የሚመጥን የተማሪዎችን ግላዊ እድገትን እና የመማር እድልን የሚደግፍ ምላሽ መስጠት እና ተማሪዎችን በተቻለ መጠን በመደበኛ የትምህርት ፕሮግራማቸው እንዲጠመዱ በሚያደርግ የት/ቤት ሥነ ሥርዓትን/ዲስፕሊን መምራት።

i) መምህራንን እና ሌሎች የሥራ ባልደረቦችን ስለ እያንዳንዱ ልጅ ፍላጎት፣ የመማር ዘይቤ፣ እና የእድገት ስኬት/ክንዋኔ እንዲኖራቸው አግባብነት ያለው መረጃ/ኢንፎርሜሽን እንዲለዋወጡ በማበረታታት ከአንድ የክፍል ደረጃ ወደ ሚቀጥለው ለልጆች ምቹ የሆነ ሽግግር እና የእርምጃ ሒደት በመፍጠር ዝግጁነትን ማሳደግ።

j) በየትኛውም አስፈላጊ ቦታ ላይ ኮሙኒኬሽንን/ግንኙነትን በማህበረሰቡ ውስጥ በሚነገር ቋንቋ ያመቻቻል።

k) ልጆች ከቤታቸው ውጪ፣ ከቤተሰብ እንክብካቤ ወይም ከልጆች እንክብካቤ ማዕከላት፣ እና ከቀዳሚ ት/ቤት ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም፣ ሽግግር እንዲያደርጉ መርዳት፣ የእያንዳንዱን ልጅ አስተዳደግና አካዳሚያዊ ክንውን መደገፍ፣ እና ለእያንዳንዱ ልጅ የረዥም ጊዜ የትምህርት ግቦችን የሚተገብር/የምትተገብር እቅድ በማዘጋጀት የቤተሰብና የት/ቤት ግንኙነት/አጋርነት ወሳኝ ስለሆነ ማመቻቸት።

l) የት/ቤት ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች የተለያየ ዓይነት የት/ቤት ማህበረሰብን የሚያንፀባርቅ መሆኑን ማረጋገጥ እና ሁሉም የአካዳሚ ፕሮግራሞች እና የት/ቤት እንቅስቃሴዎች ለሁሉም ተማሪዎች በእኩልነት ሚዛን እንዲዳረስ መሥራት።

2. *ሥርዓተ ትምህርት፣ ማስተማር፣ እና መገምገም*

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለካሪኩለም፣ ስለ ትምህርት፣ እና ስለ መመዘኛ ያለው አቀራረብ ለሁሉም ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን ከፍተኛ ስኬት ታሳቢ ተደርጎ የእያንዳንዱን ወጣት ተማሪ ፍላጎት ማሳካት። መምህራን የተማሪዎችን ሰፊ ችሎታዎች፣ የአስተዳደግ ደረጃዎች፣ ፍላጎቶች፣ የበፊት ታሪኮች፣ የመማር ዘይቤዎች፣ እና ልምድ/ተሞክሮዎች፣ በማስተናገድ እና በተማሪዎች ህይወት የራስ ማንነትን የሚያንፀባርቅ ቀዳሚ ስኬቶችን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መቆጣጠር የሚቻል ተግዳሮቶችን ያቅዳሉ/ይተገብራሉ።

a) የተማሪ ስኬት የሚወሰነው የልጅን ሁለንተናዊ ፍላጎት የሚያሟላ ቀጣይነት የሚኖረው ከሪኩለም በመተግበር ይሆናል። ቀዳሚ የልጅነት እና የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ከሪኩለም ከቦርድ ፖሊሲ/Board Policy IFA የሚጣጣም ሆኖ ከሪኩለም፧ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩል ደንብ/MCPS Regulation IFA-RA ከሪኩለም፧ እና የሚከተሉትንም ያካትታል፦

(1) የተጻፈው ሥርዓተ ትምህርት፣ በሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍና በሥርዓተ ትምህርት መመሪያ ላይ እንደቀረበው

(2) የተማሩት ከሪኩለም፣ ምንባብ/የቋንቋ ስነጥበብን ጨምሮ፣ ሒሳብ፣ ማህበራዊ ጥናቶች፣ ሳይንስ፣ ስነጥበብ፣ ሙዚቃ፣ እና የአካል ጥንካሬ ትምህርት፣ መምህራን ከተማሪዎች ጋር ተግባራዊ እንዳደረጉት

(3) የተማሩት ከሪኩለም/ሥርዓተ ትምህርት፥በተማሪ ክንውን ግምገማ ላይ እንደታየው፥

(4) እየተካሄደ ያለው የሙያ ማበልጸጊያ የሚያስፈልገው ቀጣይነት ያለው ትግበራ፣ ክትትል፣ እና ቁጥጥር

(5) በመምህራን፣ በአስተዳዳሪዎች፣ እና በማዕከላዊ አገልግሎት ሠራተኞች አማካይነት የከሪኩለም/ሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ክትትል ማድረግ

b) የማስተማር ተግባሩ በርካታ ዘዴዎችን፣ስትራተጂዎችን፣ እና ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ ሆነው እንዲማሩ የሚያበረታቱ ስልቶችን አጣምሮ ይይዛል። እንደዚህ ዓይነት ተግባሮች አግባብነት ካላቸው የቦርድ ፖሊሲዎችና ከ MCPS ደንቦች/መመሪያዎች ጋር የሚጣጣሙና የሚከተሉትን የሚያካትት፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም፣ የቦርድ ፖሊሲዎች/Board policies IKA የማርክ አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረግ IOAልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ ትምህርትIOD፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች፣ እና IOB፣ ስንክልና ያለባቸው ተማሪዎች ትምህርት፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ/MCPS Regulation IHB-RA የት/ቤት የአካደሚክ ቡድን አሰራር

ልምድ።

(1) ቴክኖሎጂን ከከሪኩለም፣ ከማስተማርና ከመመዘኛ ጋር በማዋሃድ በተማሪ ጥንካሬ ወይም ዝንባሌ ላይ ለመገንባት ወይም የተማሪን ችሎታ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ማጠናከር።

(2) የፕሮግራሞችና የትምህርት አሰጣጥ ውሳኔዎች የሚመሠረቱት የተማሪ የትምህርት አፈጻጸም/ክንውን መረጃ በተደራጀ ስታንዳርድ/መለኪያ አንፃር ተተንትኖ ነው።

(3) የተለየ የማስተማሪያ ልምዶች የተማሪን አፈጻጸም ለማሻሻል እንዲረዳ፣ ለማዳበር፣ ለማፋጠን እና ሌሎች ስልቶችን/ስትራተጂዎችን እንደአስፈላጊነቱ የተማሪ የአካደሚክ እምቅ ችሎታ ለማሳካት መርዳትን ያካትታል። እንዲህ ዓይነት ተሞክሮዎች በተማሪዎች መካከል የመማር ዘዴዎችን እና የአካል፣ ማህበራዊ፣ እና ስሜታዊ ልዩነቶችን ይፈታል።

(4) ለቀዳሚ የልጅነት እና የአንደኛ ደረጃ ፕሮግራሞች፣ የማስተማር እቅድ ዝግጅትና ትግበራ ላይ፣ በአጠቃላይ ትምህርት፣ በልዩ ትምህርት፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ትምህርት፣ እና ከአጠቃላይ ትምህርት ጋር ለተጣመሩ ሌሎች ትምህርቶችና ድጋፎች ፕሮግራም የሠራተኞችን ልዩ ችሎታ ይጠቀማሉ።

(5) የማስተማር ተሞክሮዎች

(a) የህጻናትን የእድገት ፍላጎቶች ለማሟላት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ለመጠቀም ቁሳቁሶችን እና መገልገያዎችን ማዘጋጀት፣

(b) በእጅ እየሠሩ የሚማሩበት እንቅስቃሴዎች ላይ፣ የልጆች የህይወት ተሞክሮዎች፣ ተጨባጭ እቃዎች/ቁሶች፣ እና ማመሳሰያዎች ላይ አጽንዖት መስጠት፣

(c) ልጆች የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን/activities እንዲያደርጉ ምርጫዎችን እና እድል መስጠት፤

(d) ጨዋታ (የታቀደ እና ድንገተኛም ቢሆን) ልጆች እንዲማሩና እድንዲያድጉ ዋጋ ያለው መፍትሔ መሆኑን ግንዛቤ መስጠት፣

(e) እድሎቹ የሚሰጡት የልጆችን ተነሣሽነት፣ ኃላፊነት፣ በራስ መተማመን፣ እና ነፃነታቸውን ለማዳበር የሚረዳቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣

(f) ለልጆች የመሪነት እድል መስጠት፣ እና

(g) ልጆች ከአዋቂ ሰዎች ጋር እና ከእኩዮቻቸው/ጓደኞቻቸው ጋር በቋንቋ ለመግባባት እና ለመነጋገር እንዲችሉ እድል ለመስጠት የማንበብና የመጻፍ ችሎታን በመገንባት ሁሉንም ትምህርትና እንቅስቃሴዎች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር በቋንቋ-የዳበረ አካባቢ መፍጠር።

c) ፋይዳውን መፈተሽ

የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy IKA፣ ስለ ማርክ አሰጣጥና ሪፖርት ማድረግ፣ የትምህርት እርምጃን መመዘን የማስተማር ዑደታዊ ገፅታ አስፈላጊ አካል መሆኑን ይደነግጋል።

(1) መምህራን ቅድመ-መመዘኛዎችን፣ ፎርማቲቭ መመዘኛዎችን፣ እና ድምር/ማጠቃለያ መመዘኛዎችን የሚጠቀሙት ስኬትን አስመልክቶ ከወላጆች/ሞግዚቶች እና ከተማሪዎች ጋር ለመገናኘት፣ የትምህርት ግብ ለመድረስ የትምህርት አሠጣጥን ለማቀድና ለመስጠት፣ ለአፋጣኝ አግባብ ያለዉ ጣልቃገብነት፣ ተማሪዎች ለሚሠሩት ሥራ ወቅታዊ የሆነ ምላሽ ለመስጠት፣ እና ተማሪዎች እንዲማሩና እውቀታቸውን እንዲያሳዩ ተጨማሪ እድሎችን ለመስጠት ነው።

(2) የካውንቲ፣ ስቴት፣ እና ብሔራዊ ደረጃዎችን የጠበቀ/ተመጣጣኝ የሆነ አጠቃላይ የመመዘኛ ፕሮግራም የሚከተሉትን ያካትታል:-

(a) በየጊዜው በተለያዩ መመዘኛዎች የተማሪን ሥራ ማሳየት።

(b) ተማሪዎች የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅመው ብቃታቸውን እንዲያሳዩ እድል ይሰጣል።

(c) ለተማሪዎች እና ለወላጆች/ሞግዚቶች ተማሪ የደረሰበትን ደረጃ ትርጉም ያለው ምላሽ/feedback፣

(d) ለወላጆች/ሞግዚቶች እና ተማሪዎች ስለ ደረጃ አሰጣጥ መስፈርት ግልጽና ወቅቱን የጠበቀ ኮሙኒኬሽን/ግንኙነት።

(e) በት/ቤቶች ውስጥ እና በት/ቤቶች መካከል ዘላቂነት/ወጥነት።

(3) ድጋሚ ማስተማር እና ድጋሚ መመዘኛ መስጠት የተማሪን መማር ያነሣሣል እናም በተማሪው(ዋ) ልዩ ፍላጎት/ሁኔታ ላይ ያተኮረ የማስተማር ሁኔታን ያሟላል።

3. ድርጅታዊ መዋቅር

a) ወደ ከፍተኛ - ክንውን የሚደርስ ቀዳሚ የልጅነት እና የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም ድርጅታዊ መዋቅር -

(1) በማህበረሰቡ ውስጥ የልጆች እንክብካቤ ሰጪዎች እና ኤጋር ኤጀንሲዎች ጋር እንዲሁም ሌሎች የማህበረሰብ አገልግሎት ሰጭዎች ጋር በመተባበር ለወጣት ልጆች እና ለወላጆቻቸው መሠረታዊ/አስፈላጊ አገልግሎቶችን እንዲቀጥሉ ለማድረግ የካውንቲ፣ የስቴት፣ እና የፌደራል መገልገያዎችን/resources ውጤታማ በሆነ ሁኔታ መጠቀም።

(2) የትምህርት ጊዜን ይበልጥ መጠቀም/አሟጦ መጠቀም፣ እና

(3) የተማሪ ሽግግር፣ ምደባ፣ እና የፕሮግራም ቀጣይነትን በእያንዳንዱ የልጆች የእድገት ደረጃ፣ ከቤት፣ ከህጻናት እንክብካቤ/child care፣ ወይም ከቀዳሚ ት/ቤት ወደ ሙዓለ ህፃናት/pre-K፣ እንደአስፈላጊነቱ እና ከአንዱ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ክፍል ወደ ሌላኛው ማመቻቸት እና አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ልጆች ለይቶ ማወቅ።

b) ውጤታማ፣ እንደሁኔታው ለመቀበል የሚያስችል፣ እና ተባባሪ የሆነ ድርጅታዊ መዋቅር የሚያካትተው፥

(1) በጥራት የሚሰጡ ቀዳሚ የሕጻናት ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች መኖራቸውና ጠቀሜታዉን እና ለዉጤታማ ተደራሽነት፣ ለቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች እና ለፕሮግራሙ ብቁ ከሆኑ ተማሪዎች ቤተሰቦች ጋር ግንኙነቶችን መገንባትን በሚያካትት መልኩ የህብረተሰቡ ግንዛቤ፣

(2) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መምህራን በየደረጃው - ቡድኖች ጋር፣ በትምህርት ዓይነት፣ እና ከልዩ ትምህርት እና አጠቃላይ ትምህርት ፕሮግራም ሠራተኞች ጋር የሚተባበሩባቸው እድሎች፣

(3) ሠራተኞች ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር ተገናኝተው ስለተማሪ ግስጋሴ ለመወያየት ያሏቸው እድሎች፣

(4) ውጤታማ የሆነ የመለየት፣ ጣልቃ መግባት፣ እና የማዳበር/የማበልፀግ ፕሮግራሞች (effective identification, intervention, and enrichment programs)

(5) በሁሉም የሥርዓተ ትምህርት/ካሪኩላር ዘርፎች በቂ የማስተማር ጊዜ፣

(6) ተማሪዎች ከአንደኛ ደረጃ ወደ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሲገሰግሱ በእያንዳንዱ ተከታታይ ክፍል ቁልፍ የሆኑ ለትምህርት እና የእድገት አብይ እመርታ እንዲኖራቸው የሚያዘጋጃቸው አጠቃላይ የትምህርት ፕሮግራም።

c) ትንንሽ ልጆች በቀላሉ ትልቅ ሰው ለማግኘት መቻላቸው በጣም አስፈላጊ መሆኑን ሙሉ ግንዛቤ በመውሰድ ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት መማሪያ ክፍሎች በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር - ለአዋቂ ተመጣጥኖ ይመደባል።

(1) የግንዛቤ/ማወቅ እና ስሜታዊ እድገትን መደገፍ፣

(2) ጎልማሶች-ከ-ልጆች እና ልጆች-ከ-ልጆች ጋር የሚደረግ ተግባቦትን ማስፋት፣

(3) ግለሰባዊ እና አነስተኛ ቡድን የትምህርት ተሞክሮ፣ እና

(4) አስፈላጊነቱ ከፍተኛ ለሆኑ ት/ቤቶች የተለየ ድጋፍ ማድረግ፡፡

4. አመራር እና እቅድ

የመማር ማስተማር ሂደቶችን በተከታታይ ለማሻሻል አስተዳዳሪዎች፣ መምህራን፣ እና ድጋፍ የሚሠጡ ሠራተኞች ዕውቀታቸውን፣ ችሎታቸውን/ሙያቸውን ያዳብራሉ። በፕሮግርም እና በት/ቤት ደረጃ የ ሒደት ሥርዓት መኖር አለበት ለ--

a) ፕሮግራምን፣ ት/ቤትን ወይም የመማሪያ ክፍልን ራዕይ፣ ተልእኮ፣ ግቦች፣ እና መርኃ ግብሮችን መቆጣጠርና ግንኙነት ማድረግ፣

b) ራዕይ መፍጠር እንዲችሉ ለመርዳት ከባለድርሻ አካላት ጋር መሥራት እና በከፍተኛ ደረጃ የሚሠሩ ድርጅቶችን የሚደግፍ በተከታታይ የሚሻሻሉ ስልቶች/ስትራተጂዎች ላይ በማተኮር

ተግባራዊ ማድረግ ፣

c) የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማጎልበት በተነደፈው የሙያ ብቃት ማሳደግ/ማዳበር እድሎች እንዲሳተፉ አቅም ያላቸውን መሪዎች ለይቶ ማወቅና፣ እና

d) ራዕዩን፣ ግቦቹንና የተግባር እቅዶቹን በማከናወን ሁሉም ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ የሚጠብቁት ዓይነት ፕሮግራምና የት/ቤት ሠራተኞችን ችሎታ ለማጠናከር የሚያስችል ውስጣዊ አቅምን መገንባት።

5. ወላጅ/ሞግዚት እና የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ግንኙነት

ከቦርድ ፖሊሲ/Board Policy ABA ጋር የሚጣጣም የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ ፖሊሲ/Policy ABC፣የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ፣እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/MCPS Regulation ABC-RA፣ የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ፣ የልጆችን የማህበራዊ እና የአእምሮ እውቀት ለማሳደግ ወላጆች/ሞግዚቶች እና የማህበረሰብ አባላት እጅግ በጣም አስፈላጊ አጋሮች ናቸው። የቤተሰብ እና የት/ቤት ሚና ቁርኝት ግንኙነትንና በጋራ መወሰንን ያካተተ ትብብር ያስፈልገዋል። ይህ ተጓዳኝነት/አጋርነት እመርታን የሚጨምረው፦

a) እንደየአስፈላጊነቱ ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የአንደኛ ደረጃ ፕሮግራም ህፃናት ልጆችን ከቤት፣ የህጻናት እንክብካቤ/ጥበቃ፣ የቤተሰብ የቀን ውሎ/እንክብካቤ፣ ወይም ቀዳሚ ት/ቤት፣ ሽግግር ወቅት ላይ ቤተሰብን እና ህፃናትን የሚረዳ ግንኙነት እና ማዳረስ/outreach፣

b) ልጆቻቸው በት/ቤት እና በኑሮአቸው ስኬታማ የመሆን ችሎታን ከፍ ለማድረግ ወላጆች ያሏቸው እድሎች፥

c) በቤተሰቦች እና በት/ቤት መካከል ዘወትር የሚደረግ ሁለትዮሽ ግንኙነት ስለ እያንዳንዱ ልጅ ግላዊ ግስጋሴ በሚመለከት፣ ስለ አካባቢ ት/ቤት እና ስለ ሥርዓቱ ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ ፕሮግራሞች እና ስለሚደረጉ ነገሮች መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለመለዋወጥና ምላሽ ለመጠየቅ፣

d) የቀዳሚ ትምህርታዊ/አካደሚክ ስኬትን ለመደገፍ በማህበረሰቡ መካከል ከሚገኙት ባለድርሻ አካላት ለምሳሌ፦ የአካባቢ የንግድ ተቋማት፣ የህብረተሰብ ድርጅቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ እና እንደ ቤተመጻህፍት/ላይብራሪዎች የመሣሠሉ ሌሎች ኤጀንሲዎች ጋር መተባበር፣ እና

e) ለቤተሰቦች እና ለማህበረሰብ አባላት በቀዳሚ የህፃናት ልጆች እና ት/ቤት ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች፣ እንቅስቃሴዎች፣ እና ዝግጅቶች ከህፃናት ጋር ተሳትፎ ለማድረግ በርካታ እድሎች

6. የሰብአዊ ሃብት/Resources እና ሙያ ማበልጸግ

ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለቀዳሚ የሕጻናት እና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ሠራተኞችን እውቀት ያላቸው፣ ችሎታ/ሙያ፣ እና የሁሉንም ትናንሽ ልጆች ፍላጎት ለማሟላት የሚያስፈልገውን የኤክስፐርት ሙያ የተካኑትን ይመለምላል፣ ይቀጥራል እናም በስራ ላይ ያቆያቸዋል።

a) የሥራ ባልደረቦች ማለት፦

(1) ስለወጣት ልጆች የአስተዳደግ ሥነምግባር እውቀት ያለው/ያላት፣

(2) ሁሉም ልጅ ለመማርና ስኬታማ ለመሆን ይችላል/ትችላለች በሚለው ፅንሰሐሳብ በቁርጠኝነት የሚያምን/የምታምን

(3) ቅን የሆነ መልካም ግንኙነት ከተማሪዎች እና ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር የማዳበር ችሎታ እና በትምህርት ሒደቱ እንዲሳተፉ በማድረግ የተካነ(ች)

b) የሥራ ባልደረቦች/ሠራተኞች ከሁሉም ተማሪ በከፍተኛ ደረጃ የሚጠበቅ መሆኑን ያሳውቋቸዋል።

c) ከቦርድ ፖሊሲ/Board Policy ACA ጋር በማጣጣም፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትህ/እኩልነት፣ እና የዳበረ ባህል፣ ለመመልመል፣ ለመቅጠር፣ላመያዝ/ማቆየት እና ስብጥር የሥራ ግብረኃይል ለማስፋፋት እንቅፋት የሚሆኑትን መዋቅራዊ እና ድርጅታዊ መሰናክሎችን ለማስወገድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አሉታዊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

d) የሠራተኛ ምርጫ ሲደረግ የእያንዳንዱ ፕሮግራም እና ት/ቤት ፍላጎት ግምት ውስጥ ይገባል።

e) ለፕሮግራም እና ለት/ቤት ሠራተኞችና አስተዳዳሪዎች ተከታታይ የሙያ ማበልጸጊያ

(1) ቀዳሚ የህፃንነት/ልጅነት እድገትን በሚመለከት የሥርዓተ ትምህርት/ከሪኩለም ይዘትን፣ ቴክኖሎጂን በአግባቡ መጠቀምን፣ እና የትምህርት አሠጣጥና የማስተማር ልዩነት ላይ፣ ጥልቅ እውቀት እንዲኖራቸው፣ እና

(2) የህጻናት ልጆችን ስኬታማነት ለማሳደግ ከሁሉም ወላጆች/ሞግዚቶች ጋር ለመገናኘት እና እንዲሳተፉ ለማድረግ ውጤታማ ስልቶችን ይሰጣል።

## D. የተፈለጉ ውጤቶች

ከፍተኛ ጥራት፣ ቀዳሚ የህፃንነት እና የአንደኛ ደረጃ ፕሮግራሞችን አጠቃሎ የያዘ በአዳጋች የቀዳሚ የህፃንነት እና የአንደኛ ደረጃ ተሞክሮዎች እያንዳንዱን ህፃን ጠንካራ መሠረት እንዲኖረው/እንዲኖራት የሚያደርግ እና ከአንደኛ ደረጃ/ኤለመንተሪ እስከ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሲገሰግሱ፣ ከዚያም አልፎ በህይወት ዘመናቸው የአከደሚክና ግላዊ ክንውኖችን ቁልፍ የትምህርት እና የእድገት ውጤቶችን በእያንዳንዱ ተከታታይ ደረጃ ለማግኘት እንዲችሉ

## E. ክለሳ

ይህ መመርያ የሚገመገመው በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሰረት ነው።

***የመመርያ ታሪክ፡-*** የፀደቀበት ውሳኔ ቁ. በውሳኔ ቁ. 345-88፣ ጁን 27/1988 ተሻሽሏል። በውሳኔ ቁጥር 284-07፣ ሜይ 21/2007 የቴክኒክ ማሻሻያዎች ተደርገዋል። በውሳኔ ቁጥር 319-17፣ ጁን 26/2017 ተሻሽሏል። 205-18፣ ኤፕሪል 12/2018

***ያስታውሱ፡-*** ከውሳኔ ቁጥር 345-88 በፊት ይህ ርእስ ይመራ የነበረው በሚከተለው፡- K-8 ፖሊሲ፣ በውሳኔ ቁጥር 161-80 ፌብሩሪ 12, 1980 ፀድቋል፣ የማሻሻያ ውሳኔ ቁጥር 912b-83፣ ኖቨምበር 8/1983 ዳግመኛ ተሻሽሏል፣ በውሳኔ ቁጥር No 333-86 ጁን 12, 1986 እንደገና ተሻሽሎ ወጥቷል፣ እና የውሳኔ ቁጥር 458-86፣ አገስት 12, 1986፣ በውሳኔ ቁጥር 345-88, ጁን 27, 1988 ተሽሯል። የቦርድ ፖሊሲ/Board policy IEF መርህ፣ ቀዳሚ የሕፃንነት ትምህርት፣ የተጣመረው በውሳኔ ቁጥር 205-18፣ የዚህ ፖሊሲ ማሻሻያዎች የተሻረው የተሻሻለው የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy IEA ኤፕሪል 12, 2018 በፀደቀ ጊዜ ነው።